# እ.ሞ.ታ.ለ.ሁ.

**በስሜ ታደሰ**

**ርዕሴን የደረጀ ለማድረግ አራት ሁነኛ መረጃዎችን አስቀድሜያለሁ፡፡**

## መረጃ አንድ

ስለ ሞት መምከር ግድ መሆኑን በዓለም አቀፍ ደረጃ ወረርሽኝ በመሆን አለምን እያስጨነቀ ባለበት ግዜ ላይ ሁላችን አለን፡፡ ኮቪድ19-ኮሮና ቫይረስ፡፡ ይህ ወረርሽኝ በአንዳንዶች ቅድመ ትንቢያ ተሰጥቶበት እንደነበር ቢነገርም እርግጡ ግን በአመዛኙ ድንገቴ መሆኑ ነው፡፡ በሽታው በአሁኑ ወቅት ከአምስት ሚሊዮን በላይ ተጠቂዎችን ያስቆጠረ ከሦስት መቶ ሺህ በላይ ሰዎችን ወደ ሞት ያጉዋጉዋዘ የጤና ችግር ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ወረርሽኝ እኔም ሆንኩ ብዙዎቻችን ስለ ሞታችን በቅጡ እንድናስብ ገድ ብሎናል፡፡

ይህ ወረርሽኝ ያለልዩነትሁሉን አስተናግዱዋል፡፡ያለቀለም፣ያለዘር፣ያለፆታ፣ያለብሔር፣ያለ እድገት፣ያለትምህርት ወዘተ ልዩነት ሞት ሁሉን አስተናግዱዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ እ.ሞ.ታ.ለ.ሁ. በማለት ይልቤን ጬኸት ባሰማ ተገቢ ነው፡፡

## መረጃ ሁለት

ከ‹‹ከየቦሲኒያዎች››የተረት ማድብል ውስጥ አንዱን እነሆ፤ -‹‹ሰውየው እግዚአብሔር ‹ዛሬ ትሞታለህ !››ባለው ጊዜ ተጦሪውበማደናገጥ‹‹ፍትህ የለማ!! እንዲህ ያልከኝ እውነት ከልብህ ነውወይ ?! እውነት አንተ እግዚአብሔር ሆነህ ይህን ካደረከውፍርደ ገምድል ነህ !››አለው፡ ፡

ይልቅኑ ሰውየውበተነቃቃ ሁኔታ እግዚአብሔርን ሊያሳቅል ሞከረ፡ ፡ ሁዋላ ላይ ግን ጥያቄ እና ሜሉሱ አቅጣጫእንዳያዘ፣ ረገብ ብሎ ወደ ልቡ ማለስ ሲል ‹‹እንግዲህ ምን አድርጋለሁ ውሰደኛ !›› ያለበትን ተረት ተረት ከወዳጄ ከአቶ ተሻገር ሞላ ከዓመታት በፊት ሰምቼ ነበር፡ ፡

***

የሰውየውቀዳሚየመጣት ቃል‹‹እንዴት እንድዘጋጅበት፣ ለምን ቀደምብለህ አልነገርከኝም፤

ሌላውቢቀር ከአሞት በፊት ብትነግረኝ ምን ነበረበት? !››የሚለውቀዳሚውቃሉ ነበረ፡ ፡

ለዚህ የእግዚአብሔር ምላሽ ‹‹ነግሬያለሁ፤ ማስጠንቀቂያምአንድ ግዜ ብቻ ሳይሆን ደጋግሜ ልኬልሀለሁ!፡ ፡ የሚል ሆነበት፡ ፡

ቀጣዩ የሰውየ ውጣግት ሜላኩን ቀይሮ፤ -‹‹ታዲያ እኮ ያላጠናቀቁት ሥራ አለ፤

**አንተ ራስህ ቤተሰቤን እንዳስተዳድር የጣርከኝን በውጉ አልተወጣሁም፤**

**ሰውን ሁሉ እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ ብለህ የጣርከኝን በውጉ አልሰራሁትም፤**

**‹ከሰውእኩል› ልሁን ብዬ የጀሚርኩትን ፕሮጀክት አልጨረስኩም፤**

**ከዚህምበላይ እኔ እኮ ‹አንተን ማክንያትያዊነህ ብዬነውእስከ ዛሬ ስለ አንተ ስማክር የኖርኩት፤**

**ፀሎቴን ሰምተሀል እያልኩነ ውሳማሰግንህ የኖርኩት፤**

**ሁሉን ቻይ ሚሆንህን አምኜ ይህንኑ ለሰውሁሉ ስናገር ነውየኖርኩት፤**

**ዛሬ ግን ዋሽህ አንድምማስጠንቀቂያ እንደምትወስደኝ አልላክልኝምእናምበዚህ ሜኩዛሬ ልሞት አይገባምቅድምእንዳልኩአላስጠኑ ቀቀኝም› አለው ፡**

***

እግዚአብሔርም ተጠሪውን እንግዲህ ልብ ብለህ ስማ!

--በሩጫተወዳድረህ የዛሬ ሀያ አሞት አንድኛ ወጣህ፤

የዛሬ አስራ ስድስት አሞት ደግሞሦስተኛ ወጣህ፤

የዛሬ አስራ ሁለት አሞት አስረኛ ወጣህ፤

በቅርቡ ውሬ(የሜጨረሻ) ወጥተህ ስታዲየ ሙከተዘጋህ በሁዋላ ደረሰክ ይህ የሆነ ውበአንተ ነው ፡ ››

--ከሠላሳ ዓሞት በፊት ማኑ ጤነኛ ነበርክ፤ -

ከጥቂት አሞታት ወዲህ ግን ‹ደሜከፍ አለ፣ ስኳሬ ጨምሯ፣ አይኔ እይታውን ቀነሰ፤ እያልክ ሜድሀኒት ሜውሰድህ ከጀሚርክ ሰነበትክ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በተደጋጋሚሆስፒታል ተኝተሀል፡ የአይንህ እይታ በማ ፅር ሚታገዝ የጀሚረውከአሞታት በፊት ሚሆኑን ታውቃለህ፤ አሁን ማ ፅሩምኖሮ እይታ ማኑ አይደለማ›

***

--በወጣትነትህ ግዜ ፀጉርህ ማኑ ደግሞምፍፁምጥቁር ነበር፤

ከቅርብአሞታት ወዲህ ነጭእና ጥቁሩ ማሳ ለማሳ ነው፤

ዘንድሮ ደግሞነ ጨበርከቶብሀል፡ ፡ ››

‹‹ቀድሞያለምንምማስታወሻ የተቀበለከውን ቀጠሮ በቀኑ በሰዓቱ አክብረህ ማንምሳያስታውስ ትገኝ ነበር፤ በዚህምተደንቀህበት ነበር፤

አሁን ግን ልጆችህን አስታውሱኝ ማላት አብዝተሀል፣ በድግግምትረሳለህ፤

ወዳጆችህን የት እንደተዋወቅ ማን ይባሉ እንደ ነበር ዘንግተህ ስማቸውከአፋቸው እንዲወድቅልህ ‹‹ተዋወቁ›› ማለት ከጀመርክ አሟት አስቆጥረሀል..እንደዚያምአርገህ ጆሮ የማስማት አቅሟ ስላጣያሉትን ሳትሰማያማለጠግዜ ብዙ ነበር፤

እነ ዚህ ሁሉ እኮ ቀደምብዬ መንገሬን ያረጋግጣል፤ ደግሞስ ሰውን እንደ ራስህ ለሞውደድ ጊዜ ሚፈለግህ፣ እኔ ውየ ሰጠሁን አደራ ለሚጨፈስ ሌላ ግዜ ማጠየ ቀህ ቀድሜመጥኼ የሰጠሁ እድሜመቼ አንሶ ነው! በል !‹ተነ ስ›› አለውሰውየ ወምአላንገራገረምበእሽታ ‹‹ተነ ሳ›. በማለት የጥንቱ የቦሲኒያ ተረት ታሪኪን በሞት ላይ ይደሙድሜል፡ ፡

***

**መቼምቢሆን እግዚአብሔር ፍርደ ገምድል አይደለም ፡**

**እግዚአብሔር ያላሰወቀውን ቀድሞያልተናገረውን አያደርግም፤**

**እግዚአብሔር በእውነ ትምፃ ድቅ አምላክ ነው ፡**

**ልዑልምአምላክ ነው ፡ ፈቃዱን ብቻ ፈፃሚ ፡**

ዶክትር የሸጥላ መንግሥቱ‹‹ሕዝቤን አፅናኑ››በማለት በ1997 ፅፎ ያስነ በበን መፅሐፍ ለዚህ ሚልእክቴ እንደ ሁነ ኛ ግብዓት ተጠቅሜበታሁ፡ ፡ እርግጥእርሱ ባሳተማበት በ1997 አመተ ምህረት እኔ ምበሞት ሸለቆ መካከል አልፌበት ነበርና ስለ ሞት ለመናገር ሌላ ተጨማሪ አቅምን ይሰጠኛል፡ ፡

መፅሐፉ ላይ ‹‹ሞት የሰውሁሉ እጣፈንታ ነው ፡ ››በማለት ‹‹የ ሞት አይቀሬነ ትን›ን አስረግጦ ይናገ ራል፡ ፡

ታዲያ ያኔ ምሆነ ዘንድሮ ሰዎች ‹‹ተራ ሞት››በሚሉት የሞት ገጠመኝ ላይ ብዙ ቁብ አይሰጡም› ሁሌም የተለመደ ነ ውከማለት አያልፉምበማለት የምክር እና የማስሰቢያ ቃሉን በሚጃ ያስደግፋል፡ ፡

በቅርቡ በኢትዮጵያ፤ - የኢትዮጵያ አየር መንገ ድ በይንግ መብረር በጀመረ በስድስት ደቂቃ ውስጥተከስክሶ አንድ መቶ ሀምሳ ሰባት(157) ሰዎች ሞተዋል፡ ፡ ይህን በሰማን ግዜ የብዙዎቻችን ቀልብ ግፍፍ ብሎነ በር፡ ፡ (በነ ገ ራችን ላይ ከእነ ርሱ መካከል የጌታቸውበለጠ አንድ ልጅ ነ በረበት፤ አ ሲዲራቅ ጌታቸውበለጠ፤ ልጄ ከሚሄፉ በፊት በፌስ ቡክ ገፁ ‹‹ሩጫውን ጨርሻለሁ›› ብሎምነ በር፡ ፡ )

***

ብዙዎቻችን እንዲህ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ማለቃቸውን ስንሰማእንደነ ግጣለን፣ ወቅያኖስ ዋጣቸው፤ ተረሸኑ፣ ተቃጠሉ፣ ጎርፍ አጥለቀለቀቸው...››ስንባል መግቢያ እናጣለን፡ ፡

ብንብከነ ክንም ይህን የማሉ ‹‹ሞቶች›› በየቀኑ በዓለምላይ አይሆኑም ፡ እንደ ዶክተሩ ሸጥላ ገለፃ ከዚህ አስደንጋጭየ ሞት አደጋ እና የቁጥር ስሌት በበለጠ‹ ተራ ሞት››በተባለው መንገ ድ በዓለምላይ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በአንዲት ጀምበር ይሞታሉ፡ ፡ ከዚህምአለም ይወጣሉ፡ ፡

የዛሬ አስራ አራት አመት (በ1997) በነ በረውስሌት በዓለምላይ በአንድ ሰዓት 6250 ሰዎች ይሞቱ ነ በር፡ ፡ ይህ በ24 ሰዓት ሲባዛ በቀን 150 000 ሰዎች ይሞታሉ፡ ፡ ይህምበየቀኑ

የሚሆን ነበር፡፡ እንግዲህ የዘንድሮውን ከዓለምሕዝብጋር አጣጥሜ ብንቆጥረውበየቀን የትየሌሌ የሰውልጆች ይሞታሉ፡፡

***

እንደእውነቱ ከሆነ ሚዲንገጥከተገባ ማበርገግ ያለብን ለዚህ ሞት ነበር፡፡ ግና አብረን እየኖርን ነው፤ በየአጋጣሚውበዓለምላይ አንድጎረቤታችን ብቻእንደሞት በሚቁጠር ልማድ ስለኖርን ብዙዎቻችን ለሞት ምንምቁብ አንሰጥም፡

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን እያንዳንዳችን ሌላውን ቀብረን ስንማለስ በተራችን እኛም የምንቀበርበት ቀን ሊመጣእንደሚችል የማንዘብ አቅማችን ስስ ነው፡ እንዲህምቢሆን አንድነገር ግን በየሰዐቱ ውል ሊልብን ይገባል፡፡‹‹እኔ እኮ ሟች ሰውነኝ››የሚል፡፡

እርግጥተገዳዳሪ ችግራችን ‹‹መቼ እንደምንሞት እርግጠኛውን ቀን አለማወቃችን ነው፡››

እንዲህምቢሆን ግን እርግጠኛ ባልሆንበት ጊዜ እርግጠኛ ስለሆነ ውሞት ማዘጋጀት አለብን፡፡

እንደ ዶክተር የሽጥላ መንግስቱ አነጋገር‹‹ይህ ርዕሰ ነገር አስደንጋጭቢሆንምእውነቱ እወነት መሆኑ የተረጋጠነው፡

## መረጃ ሦስት

በእድሜጠና ያሉት ሰውበሮምከተማስነ ማለኮት ለመሞር የመጣውን የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን አማኝን አግኝተውሊያነጋግሩቱ ጀመሩ፤ - ይላል ዶክተር የሽጥላ፤ -

--እዚህ ምን ልታደርግ መጣ?

--ለመሞር ነውየመጣሁት፤

--ምንድን ነውየምትመሪው?

--የክህነት ትምህርት

--ምን ለመሆን ?

--ካህን

--ከዚያስ ?

--የደብር አለቃ እሆናለሁ፤

--ከዚያስ ?

-- (ቢሳካልኝ ያንድ አገረ ስብከት ጳጳስ እሆናለሁ)

--ከዚያስ ?

--ፊቱ በደስታ ተሞልቶ‹‹በዓለምለሚገኙት ካቶሊኮች የበላይ አባት እሆናለሀ ሊቀ ጳጳስ››

--ከዚያስ ?

--ከዚያማየማይቀረውን ሞት እሞታለሁ፡፡

--ልጄ በዚህ ሁሉ ውስጥ ሞት ቀድሞእንደሚጣአስበሀል ?››

--በጭራሽ አባቴ እኔ እኮ ገና የ23 አመት ወጣት ነኝ፡ ፡

-- ‹‹ልጄ ተሚሪ ምእያለህ የሚይቀረውን ሞት ተሞታለህ፤

የደብር አለቃምእያለህ የሚይቀረውን ሞት ትሞታህ፤

ጳጳስምሆነ ህ በሚይቀረውሞት ማከራትህ አይቀርም፤

ልጄ ለምን የ ሚቃረውን አስከትለህ በሚጀሚሪያ ለሚይቀረውአትዘጋጅም›በማለት ተሰናብተውት ሄዱ፡ ፡ ( ሕዝቤን አፅናኑ ገፅ 54 1997)

***

## መረጃ አራት

እንግዲህ ከእወነ ቱ ጋር እንጋፈጥ፣ እንላተምም፣ ይህን ማጋፈጥ በ1997 የ97ቱ የፖለቲካ ውጥንቅጥ በኢትዮጵያ በሆነ ግዜ ግርግሮች በየ ቀኑ ይፈጠሩ ነበር እናምከእቴጌ ማ ን(የ ካቲት 12 ትምህርት ቤት) እስከ የሺ ደበሌ ከፍርሀት እና ከሞት ጋር ከሞት ጋር እየ ተጋልኩ በእግሬ ቤቴ ማጋባቴን አልዘነ ጋም፤ የ ዚህ ቀን ማግስት ደግሞየ ደሞዝ ቀን ስለነ በር ሒሳብ ክፍል የ ሰልፉን ተራ ተቀላቀልኩ እናምከሴቲቱ ፊት በትግስት ደረስኩ፤ - ድርሻዬን ቆጥራ ጨረሰች ልትሠጠኝ እጄዋን ስትዘረጋ እኔ ምልቀበል ዘረጋሁ፡ ፡ ፈጥኖ ግን ጭልምልምአለብኝ፤ ወደቁኝ፡ ፡ ዘርዐይ አስግዶምከሁዋለዬ ነበርና፡ ፡ ለካስ ገንዘቡን ተቀብሎልኝ ነበር ፡ ፡ ግቢውተራብሾ በትንሹዋ የአስተዳዳሪውቮልስ ከሆስፒታ ሆስፒታል አደራረሱኝ፤ በሦስተኛውጣራ ላይ ቤተዘታ ሲያደርሱኝ በትንሽ እህቴ ጩኸት በቅደስት ወደዚህ ዓለምተማለስኩ፡ ፡

እናምትረፍ ብሎኝ ከፊታችሁ ቆሚያለሁ፡ ፡ ሚቼምአንዲህ የሚያስደነ ግጥ ያስደንግጣችሁ አይባልምየ እኔ ውግን ለጥቅምሆነ ልኝ፡ ፡ በዚያን ግዜ ባለቤቴን ለማገዝ ከጎኑዋ የነበራችሁትን አልረሳም ለአከ ታፈሰን፣ ጄሪ ታየ፣ ሚኒልክ አስፋው፣ ሰለሞን ሽፈራው.፣ቅድስት ታደሰ፣ዘርአይ አስግዶም….አልዘነጋችሁም።

ታዲያ የዛን ግዜው በሞት ጥላ ስር ማለፌ በእጄ ላይ ያለውን ሳልሰጥ ሚሄድ ነበር የሚል ቁጭት ፈጥሮብኝ አልፎአል። ለዚህ ደግሞ ምላሼ ሊማ ዘሩ የ ተገ ባቸውን መፅሐፍት በማቃብር ውስጥ ማኖር ሊያስቆጩኝ እንደሚቻል በማመ ቁርጡኛ መሆንን ከጸጋው የ ተነ ሳም እንድወስን አደረገኝ ዛሬ ሰባተኛውን መፅሐፌን **የተካዳውን እውነት** ለንባብ አብቃቻለሁ ይህ ከ1997 ማግስት የሆነልኝ መሆኑን ሳስብ ሞትም ያስተምራል እላለሁ።

***

እንግዲህ ማለስ ብለን ከምካሌውጋር ሳይሆን ከእውነ ቱ ጋር እንጋፈጥ፤ እንላተም፤ በማለተሙ ውስጥ ለውጥምነ ውጥምይሁንልን፡ ፡

***

---ማኛ ችንምብንሆን ይህን የ ሚይቀረውን ሞት አንድ ቀን እንጋፈጣለን፡ ፡ እንሞታለን፡ ፡

--በራሳችንምሆነ በምንወዳቸውየቤተሰብአባላትእና ጓደኞች ላይ ሞት ድንገት ይመጣል፡ ፡

--ሞት ወደ ሰዎች በአንድ አይነት መንገድ መጥቶ ስለማያውቅ ሁሌምለሁሉም እንግዳ ይሆናል፡ ፡

--በድንገት መሞትምሆነ ቀስ እያሉ መሞት፣ የየሰውግላዊ ተሞክሮ ይሆናል፡ ፡

--በሞት አፋፍ ላይ ሳሉ ለመኖር መመኘት፣ ለመቆየት መፈለግ፣ ላለመሞት መታገል ባልተቋረጠ ሁኔታ ሁልጊዜ በየሰውውስጥ ይመላለሳል፡ ፡

በዚህምበዚያምእግዚአብሔር እውነተኛ ሆኖ ይኖራል‹‹ለመወለድ ግዜ አለው፤ ለመሞትምጊዜ አለው፤ ለመትከል ጊዜ አለው፤ የተተከለውን ለመንቀል ጊዜ አለው..››(መክብብ 3፤ 2)

እንደ እውነቱ ከሆነ ከእግዚአብሔር ግዜ ለሞት ተቆርጦለታል፡ ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ወደዚህ ዓለምየገባንበት ቀን፣ የተወለድንበት ቀን በጌታየተወሰነ እና የታወቀምእንደነበር፤ -ልክ እንዲሁ እንደገባን ከዚህ ዓለምየምንወጣበትምየምንሞትበትምግዜ የተወሰነ ነው፤ የታወቀ፡ ፡ እናምያ የተወሰነ ውጊዜ ከመሆኑ በፊት እርግጠኛ የሆነ ውአይቀሬ ሞት በእኛ ሚፀሙየማይቀር ከሆነ ማዘጋጀት ግድ ነው፡ ፡

# ታዲያ እንዴት እንዘጋጅ!!!

***

ሙሴ ‹‹በእግዚአብሔር ምክር ውስጥ ጠልቀን፣ በእርሱ ተጠምቀን››በማ ኘት ማዘጋጀታችንን የማያልጥ ሕይወት መኖር አለብን፡ ፡

ለዚህ ሕይወት ምሳሌ አድረጌ ዋቢ የምጠራውዳዊትንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፡ ፡

ዳዊት ሞት እርሱን ሳይጠራውበፊት ሁለት ልጆቹን ነበር ‹‹መጣሁ›› ብሎእያለ የወሰደበት፡ ፡

በ2ኛ ሳሙኤል 12፡ 15-24 ‹‹ሕፃኑ ልጅ በጠና ታመመ፤ ለሞት አጣጣረ፤ ዳዊት በዚህ ግዜ ፀለየ፤ ከዙፋኑ ወርዶ ማቅ ለብሶ በእግዚአብሔር ፊት ሆነ፤ እንዲምርለት ተማፀነ፤ ግን ልጁ ሞተ፡ ፡

መሞቱ በዙሪያውባሉት ሰዎች ዘንድ ሲሰማ‹‹ዳዊት ያብዳል ራሱን ይጎዳል››አሉበት፡ ፡ ይህ የታሰበውሳይሆን አባትየውልጁ መሞቱን ሲያውቅ፤ - ተነሳ፣ ታጠበ፣ ተቀባ፣ ተማጠ፣ ልክ እንደ ኢዮብ ‹‹እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔር ነሳ››(ኢዮብ 1፤ 21) በሚል ፅናት እውነትን ተቀበለ ፡ ፡ በነውጡውስጥ ለውጥ አምጪቃልምዳዊት ተናገረ፡ ፡

‹‹**...እኔ ወደ እርሱእሄዳለሁእንጂእሱወደ እኔ አይመለስም**› በማለት በመፅናናቱ እና እውነቱን በማፈጡለሌሎች የመፅናናት ምክንያት ሆነ፡ ፡ (2ሳሙኤል 12፡ 23)

ከበርካታ አመታት በሁዋላ ደግሞአቤሴሎምሞተ፡ ፡ ይህምበ2ሳሙኤል 18፤ 24-33 ላይ ይነበባል፤ -ወጣቱ ልጁየ መሞቱን ሞርዶ ሲነ ግሩት‹‹ልጄ! ልጄ! እያለ አምስት ግዜ ጮሆ አለቀሰ ፤ ሦስት ግዜ ስሙን እየ ጠራ አለቀሰ፤ ከዚያም‹‹**በአንተ ፈንታ ምነ ውሞቼ ቢሆን** ››በማለት ሐዘኑን ገለፀ፡ ፡

የዳዊት ቃል ዘሬምበወላጆች አንደበት ሲነ ገር ይሰማል‹‹ምነ ውለእኔ ባደረገው! ምነ ውእኔ እያለሁ! ምነ ውእኔን አስቀምጠህ !...››ዘሬምለልጅ ሞት የሐዘን መግለጫነው፡ ፡

***

እውነቱ ግን የእግዚአብሔር የጥሪው ሰዓት በሰውምኞት ላይ አለማንባቱ ነው፡

የዳዊት ሕይወት፤ - በእግዚአብሔር ምክር ውስጥ የጠለቀ፤ በእርሱ የተጠመቀ መሆኑን የኢየሱስ ሕይወት ከአብዘንድ ባገኘውምክሩ እንደተሞላ ምሟሟት እንችላለን፡፡

በማሰረቱ፤ - ያለንበት ዓለም‹‹መካሪ ነን !!›› ብለውእሙብን በሚኮ ሐሳዊ መካሪዎች ተሞልታለች፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ የዘመን ቁጥር እየፈጠነ 2011 ላይ ደርሰናል እርሱንምቢሆን በቅርቡ እንሰናበተዋለን፡፡ በዚህ ፈጣን በማለ ዘመን ውስጥመካሪ ከአጠገባችን ከውስጣችንም ተገማሽረውይፈታተኑናል በአማዛኙምያሸንፉናል፡፡

**አንዱ መካሪ**፤ -የብርሀን መልአክ ማስሎበየጊዜውየሚለጠውሴይጣን ነው፡ እርሱ ሁሌም በቅንነት ባንነን ልንዘጋጅ ባሰብን ቁጥር እንደ ምንሞት ትንሽ ለማስብ ስንፈልግ እሱ ቀድሞ ሐሰቱን እውነት እያስማሰለ‹‹ያደርሰሀል !››በሚል ዝንጋቴ ዕለት ዕለት የእርሱን ፈቃድ ፈፃሚ ሆነን ማሻቶ እንዲነጋ ነግቶ እንዲመሽ ያደርጋል፡፡

***

**ሌላውመካሪ**፤ - ‹‹ከራስ በላይ ንፋስ›› እያለ ‹‹የሚበጀኝን እኔ አውቃለሁ!!ባይና በሐጢያት የረከሰውእኔነታችን ነው››፡፡ ‹፣ እኔ-እኔን እየመከረ ምንምአይነት ፍሬያማሥራ ሳንሰራ ከውጤታማነት የራቀ ማንነት ይዘን እንድንኖር ይመክራል››እናም‹ልሆን እፈልጋለሁ ላልኩት ለዚያ ለማዝርጋት እንደ ዋተትኩ እግዚአብሔርን ሳላዳመጥ እኖራለሁ፡፡

***

**ሌለውመካሪ**፤ -በምንኖርት ዓለምየተዘረጋውየኑሮ ዘይቤ ነው፡ በትምህርቱ ውስጥ ያኖረው የሰውአሸናፊነት፣ በፍልስፍናውውስጥየሚ በበውየእግዚአብሔር ድርሻ አልባነት፣ በዙሪያችን ያለውጥበብየማስለውሁሉ ያሳደረብን የጭፄብን ኮተት ሞትን በላያችን ላይ ተሸክመን እንዳለን እንዳይማስለን እንዳንቀበለውይመክሩናል፡፡

***

ዳዊት ግን በሕይወቱ ውስጥ ሊመክር ከተገባውቅደሚያ ሊሰጠውየተገባውእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን በማምን እንዲህ አለ፡፡

‹‹**የ መካረኝን እግዚአብሔርን እባርከዋለሁ**››**መዝ 16፡ 7**

ዛሬ በዳዊት ቃል ተፈትሼ፣ ተሞርምሬ እንድገኝ እፈልጋለሁ፡፡

ዳዊት እረኛ ነው፤ ዳዊት ንጉስ ነው፤ ዳዊት በእግዚአብሔር እንደልቤ የተባለ ሰውነው፡

ዳዊት እግዚአብሔር ሲመክረውፈጥኖ ታዟል፡፡

ዳዊት እግዚአብሔር ሲገስፀውተፀፅቶ ይቅርታ ጠይቋል፡፡

ዳዊት ለእግዘአብሔር በፍፁምደስታ ተገዝቱዋል፤ እርሱን ብቻ አምልኳል፡፡

ዳዊት የሚገፈጠውሞት ከማምጣቱ በፊት ሁሉን በቦታ ቦታውአኑሮ የትውልድ ቀጣይነትን በአስተማማኝ ማስረት ላይ አኑሩዋል፡፡

ዳዊት በሞት ጥላ ማከከል ብሔድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉውን አልፈራም›በማለት በእግዚአብሔር መማከሩን በመኖሩ ማስክሩዋል፡፡

***

የዚህ ማጡቅልያ ቃል ‹‹የመከረኝን እግዚአብሔርን እባርከዋለሁ››የሚል ነው፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስምበሞት ጉዳና ላይ አልፉዋል፡፡ ሰውነ ወና ወደ ዓለምየገባበት ቀን የታወቀ ነው፡

ሰውነ ወና በሞት የሚለይበትምግዜ እንዲሁ የተወሰነ ነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሜልካምእረኛ መሆኑን በሕይወት ዘመኑ ከመመከከር ባሻገር ሜልካምእረኝነቱ ስለ በጎቹ ራሱን ለሞት አሳልፎ ማዘጋጀቱን ከሞቱ ቀን በፊት ማበሰሩ አስገራሚየ መኖር ማለጭውነ ው፡

ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ሀሳብ፣ በእርሱ ፈቃድ ውስጥ ራሱን ያኖረ ጌታ ነው፡

እንደ እኛ በዚች ማሪ በበዘበት ዓለምውስጥ ኖሯል፤፤ እርሱ **በዲያብሎስ ስምተመከሮ** ነበር፡፡ የብርሀን ሜልአክ ማስሎቀርቦታል፤ ተፈታትኖታል፡፡

***

--በሉቃስ 22፡ 3‹‹…አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እስቲ እነ ዚህን ድንጋዮች አንጀራ አድርግ..ብሎታ፤፡፡

--ቁጥር6 ‹‹…አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እስቲ ከዚህ ወደታች ዘለህ ውረድ››የሚል የምከር ቃል አቀብሎታል፡፡

---ቁጥር 9 ‹‹…ተንበርክከህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሀለሁ››በሎምአማክሮታል፡፡

ኢየሱስ ግን ምክሩን አልሰማም -ከዲያብሎስ ምክርን ማስማት ስለማየዋጣ፡

እርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስን ‹‹**ራሱ-ራሱን ምሞግቶታል** ‹ሐጢያት አልባውኢየሱስ ተፈትኑዋል› አባት ሆይ ፈቃድህ ቢሆን ይህን የማከራ ፅዋ ከእኔ አርቅልኝ ግን የአንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን፡፡ ›› (ሉቃስ 22፤42) ብሏል፡፡

ፀሎቱ ከራሱ ጋር ትግል ያለበት ነው፤ እኛን ለማዳን እርሱ በፍርድ ውስጥ ወደቀ፤ ሐጢያታችንን ተሸከሜ ይህንንምመቋቋምባልቻለበት ግዜ ማጎታ ማገድ ላይ ቆሞፀለየ፡፡ የእግዚአብሔር ሜልአክ ግን አበረታውቁጥር 44‹‹ልቡምበጣምተጨንቆ በብርቱ ይፀልይ ነበር››ይለናል፡፡ ራሱንምበእግዚአብሔር ምክር ውስጥአሳደረ፡፡

ኡየሱስ በፀሎቱ ‹‹እኔ ከዓለምእንዳይደለሁ እነ ርሱምከዓለምአይደሉም፤ ስለዚህ ዓለም ጠላቸው››ዮሐንስ 17፤14 አለ፡፡ በዚህም**ኢየሱስ በዓለምሥርዓት እና የኑሮ ዘይቤ አልተመከረም ፡ እርሱ** በዚህ ሁሉ ቅድሚያ የሰጠውበእግዚአብሔር አብ መማከሩን እና ፈቃዱን ሚፀማ በሚያገጥእርሱን ማምነገ ን ነው፡

***

እንዲህ ሲል‹‹…የዘላለምሕይወትምብቻህን እውነተኛ አምላክ የሆንከውን አንተንና የላከኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው..እኔ የሰጠኸኝን ሥራ ፈፅሜበምድር አከበርሁ…››(የሐንስ 17፡ 3-4) በማለት ሞትን ተጋፈጡ ፡

ዳዊት እና ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር እንዲቆዩ በተፈቀዳለቸውጊዜ ሁሉ ወደዚህ ዓለም የገቡበትን ዋንኛ ቀዳሚጉዳይ ተረድተዋል፤፡፡

--ዳዊት ሞትን በተማለከተ ስለ በልጆቹ ላይ የገለጠውማንነቱ፣

--ዳዊት ሞትን አስሜልክቶ በራሱ ላይ የተናገረውየሙተማመኛ ቃል፤

-- የዳዊት ማስናዶ ለእኛ ብትራራችን እና ምርኩዛችን ሆኖ ሊያበረታን ይገባል፡፡

ይልቅኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ትርጉምየሚሰጥን ሕይወት ኖሮ ውጤታማሆኖ የተገኘበት አቅም ተረድተን መንገዱን የራስ ገንዘብማድረግ አስፈላጊ ነው፡

***

ለሞት አለማዘጋጀትአንድንኖርበት የተፈቀደልንን አሙታት፤ -

--በማከን፣

--በሜኬቅ፣

--አስሩን ባማረር፣

--ራስን ባለማዎት፣

--ቀዳሜውን ባለማንዘብ፣

--ለእግዚአብሔር ክብር ባለሙቆም፣

--ላገኘነውድነት ምስክር ባለሞሆን፣

--ቀባሪ እንጂ ተቀባሪ ሜሆናችንን ሳንገነዘብበዋል ፈሰስ ያኖረናል፡፡

***

ይህ ለእግዚአብሔር ሆነ ለራሳችን እንዲሁምበዙሪያችን ባሉት ዘንድ ሁሉ ውጤታማትን ይዞ አይመጣም ፡ ከእርሱይልቅ በሞኖር ውስጥ፣ ቀን በተጨምርልን ቁጥር ሊቀድምየተገባውን በሞኖር መንገደኛ ሜሆናችንን ልብማለት ፤ በዚህምምድር ቋሚኑዋሪዎች ሳንሆን ተሰናባች ሜሆናችንን በሜያረጋግጥኑሮ ራሳችንን እናግኝ፤ ይህ በኑሮዋችን በተገለጠቁጥር ሞትን ለሞጋፈጥእና ለሞቋቋምፀጋውይበዛልናል፡፡ እኔ እሞታለሁእናንተስ !!አንኪያስ ሞታችን በአሸናፊነት እንዲደሞደምእ.ሞ.ታ.ለ.ሁ.የሚለውን በተከታዩ የገለፃ ምህፃረ ቃል አብራርቼዋለሁ፡፡

***

**እ**--እምነቴ በጌታ ይፀናል፡፡

**ሞ**--ሞኝነቴ በምድራዊነቴ አይገለጥ፡፡

**ታ**--ታላቅነቴ በአገልጋይነቴ ይመዝን፡፡

**ለ**--ለውጤሞቴን ያስተናግድልኝ፡፡

**ሁ**--ሁሌምሁኔታዎችን የሚቋቋምፀጋ ከጌታ ይሰጠኝ፡፡

***